በኒው ሳውዝ ዌልስ
ለ
ስደተኞች
ስለሚሰጠው አገልግሎትና
ጠቃሚ
መረጃዎች

---

ቋሚ
የስደተኞች ቪዛ

እና

ጊዜያዊ
የስደተኞች ቪዛ

ለአላቸው

ይህ ጽሑፍ ለኮምዩኒቲ ሪሌሽንስ ኮሚሽን ፎር
መልቲካልቸራል ኒው ሳውዝ ዌልስ
በ
ሪፊውጂ ካውንስል ኦፍ አውስትራሊያ
ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው

የቀረቡት መረጃዎች ጽሑፉ እስከ ተጠናቀረበት
ሚያዝያ 2004 ድረስ ወቅታዊ ናቸው

ኅዳር 2004

# ጊ ዜ ያ ዊ የ ስ ደ ተ ኞ ች ቪ ዛ
## ( TEMPORARY PROTECTION VISAS )

በዚህ ገጽ ውስጥ የሰፈሩት መረጃዎች ጊዜያዊ የስደተኞች ቪዛ ያላቸውን በተመለከተ ነው፣ የቪዛ መደብ (visa subclass) 451,477or 785).

ጊዜያዊ የስደተኞች ቪዛ (ጊስቪ) የሚያገለግለው ለ 3 ዓመት ብቻ ነው። ጊዜው ከማለቁ በፊትም አዲስ ማመልከቻ በማስገባት ቪዛው እንዲታደስለት ስደተኛው መጠየቅ ይኖርበታል።

ጊስቪ ያላቸው ሰዎች ቋሚ ቪዛ እንዳላቸው ሰዎች ሁሉ ተመሳሳይ አገልግሎት አያገኙም። በኒው ሳውዝ ዌልስ ውስጥ የሚገኙ ጊዜያው

ቪዛ ያላቸው ስደተኞች ከሚያገኙት አገልግሎቶች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

## *የማረፊያ ቦታ*

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ መረጃዎች በሚለው ርእስ ስር የተዘረዘሩት ድርጅቶች የማረፊያ ቤቶች የት የት ቦታ እንደሚገኙ ይጠቁማሉ።

ያሉበት ችግር መጠኑ እየታየ ከታች የተጠቀሱትን አገልግሎቶች መጠቀም ይችሉ ይሆናል።

። Rentstart (ሬንትስታርት) የሚባለው ሰዎች ቤት ሲከራዩ የሚሰጥ አገዛ ነው፣ ይህም ለምሳሌ፤ ለኪራይ ውል መያዣ (ቦንድ)፣ ለቤቱ ኪራይ የቅድሚያ ክፍያ ወይም ለአለብዎት ዕዳ ክፍያ የሚውል የገንዘብ እርዳታ ነው።

። አንዳንድ ጉዳዮች ሲገጥሙ እንደሁኔታው አጣዳፊነት እየታየ ጊዜያዊ የማረፊያ ቦታ የሰጣል።

የሚከተሉትን ክፍሎች ያነጋግሩ፤

**NSW Department of Housing**
(ኒው ሳውዝ ዌልስ ዲፓርትሜንት ኦፍ ሃውሲንግ) በአቅራቢያዎት የሚገኘውን የቤቶች አስተዳደር መምሪያ ጽ/ቤትን ለማወቅ ከፈለጉ በስልክ 8753 8000 ደዉለው ይጠይቁ ወይም

**Translating and Interpreting Service (TIS)** (የጽሑፍና የቃል ትርጉም አገልግሎት)፤ 131 450 ቢደዉሉ ከቤቶች አሰተዳደር መምሪያ ጋር በነፃ ያገናኝዎታል፣

ለድንገተኛ ጉዳይ፤
**The Homeless Persons' Information Centre** (የመንገድ ተዳዳሪዎች የመረጃ ማዕከል) በስልክ 9265 9081 (በየቀኑ ከጠዋቱ 9am እስከ ከሰዓት 4pm ድረስ) በመደወል ያነጋግሩ።

ይህ አገልግሎት ክፍት የማረፊያ ቦታ ያላቸውን ሆስቴሎች በተመለከተ መረጃ ይሰጣል።

## ጤንነትና ሕክምና

ጊዜያው የስደተኛ ቪዛ የያዙ ሰዎች የሚከተለውን የመንግስት ጤና አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ።

# ጊዜያዊ ሜዲኬር ካርድ **(Interim Medicare Card)**፥ (ውሃ ሰማያዊ ነው)፥ ይህን ካርድ የያዘ ሰው በነፃ (በልክ ቢል ከሆነ Bulk billed) ወይም በቅናሽ ዋጋ የዶክተር ሕክምና ያገኛል በሕዝብ ሆስፒታሎች ውስጥም እንዲሁ የተወሰኑትን ሕክምናዎች በነፃ ያገኛል፥ ይሁን እንጂ በዚህ ካርድ አንዳንድ የኮመንዌልዝ የጤና አገልግሎቶች በነፃ አይሰጡም ለምሳሌ፥ የኮመንዌልዝ የመልሶ ማቋቋም አገልግሎት (Commonwealth Rehabilitation Services) እና የአውስትራሊያ የጽሙማን አገልግሎትን (Australian Hearing Services) የመሳሰሉ ናቸው።

# የመድሐኒት ዋጋን የመቀነስ ድጎማ **(Pharmaceutical Benefits Scheme)**፥ ሜዲኬር ካርድ ያላቸው ሰዎች በሐኪም የሚታዘዘውን መድሐኒት በቅናሽ መግዛት ይችላሉ

# የጤና ካርድ **(Health Care Card)**፥ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸውና ከCentrelink አበል ለሚወስዱ የሚሰጥ ካርድ ነው፤ ይህን ካርድ የያዘ ሰው ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ ሌላ ሕክምናዎችን በነፃ ያገኛል። ነፃ የአምቡላንስ አገልግሎትና በሕዝብ የጥርስ ክሊኒክ ውስጥም የተወሰኑ አጣዳፊ ሕክምናዎችን በነፃ ሊያገኝ ይችላል።

# የጤና ጥበቃ የትርጉም አገልግሎት **(Health Care Interpreter Service)**፤ ለሕዝብ የጤና ጥበቃ አገልግሎት ትርጉም በነፃ ይሰጣል።

**ለሜዲኬር (For Medicare)**፤ በ132 011 ይደውሉ። ምክር ለማግኘት፥ ምርመራ ለማድረግና ስለአውስትራሊያ የጤና አገልግሎት ለመረዳት የሚከተለውን ክፍል ያነጋግሩ፥

**የኒው ሳውዝ ዌልስ የስደተኞች ጤና አገልግሎት**
**(NSW Refugee Health Service)**
Level 2,157-161 George St. Liverpool
ስልክ፥ 8778 0770

አዲስ ለሚመጡ ስደተኞች ተጨማሪና ልዩ የሆነ አገልግሎት የሚሰጥ ፕሮግራም አለ። ይህ ፕሮግራም ሰዎች የአካልና የስነልቦና ሕክምና ማግኘት ይገባቸው እንደሆን ይገመግማል፤ በሰፈራ ሂደት ውስጥም አስፈላጊውን ዕርዳታ ያሰጣል።
ችግር ሳይባባስ መግታት የሚባለው የስታርትስ ፕሮግራም **(STARTTS Early Intervention Program)**፥ አድራሻ፥

152-168 The Horsley Drive,Carramar2163
ስልክ፡ 9794 1900; ወይም

44-50 Auburn Rd, Auburn 2144
ስልክ፡ 9646 6666

## ትምህርት

ልጆች በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ የሕዝብ ት/ቤቶች ወይም የአጭር ጊዜ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ኮርስ በሚሰጡ ማዕከሎችና ት/ቤቶች ውስጥ ገብተው ለመማር ይችላሉ።

በስልክ፡95611000 ደውለው ስለምዝገባ ይጠይቁ
በስልክ፡9244 5324 ስለቋንቋ ማሻሻያ ፕሮግራም ይጠይቁ።

ወጣቶችም ሆኑ Gልማሶች ቴፍ **(TAFE)** በሚሰጠው የቋንቋና የሙያ ሥልጠና ፕሮግራም መሳተፍ ይችላሉ።

**የTAFE** የመረጃ ማዕከልን በ131 601 ያነጋግሩ።

## በሦ አድራሦት

ዲፓርትሜንት ኦፍ ኮምዩንቲ ሰርቪስስ **(Department of Community Services) (DoCS)** ልጆችና ወጣቶች ከጥቃትና ከጉዳት ተጠብቀው እንዲያድጉ ያደርጋል፡ ጥቆማዎችንና ሪፖርቶችን ይመረምራል፡ አስፈላጊ ሲሆንም ከወላጆች ጋር ተባብሮ በመስራት ልጆች ደህንነታቸው ተጠብቆ ማደጋቸውን ያረጋግጣል። የስደተኛ ልጆች ለአደጋ ተጋልጠዋል የሚል ጥርጣሬ ካለ ደህንነታቸውን ለመጠበቅ ዲፓርትሜንት ኦፍ ኮምዩንቲ ሰርቪስስ **(DoCS)** ሌሎች ልጆችንና ሦልማሶችን ለመጠበቅ የሚወስደውን ተመሳሳይ ርምጃ ይወስዳል።

ጥቃት ደርሶበታል ተብሎ የሚጠረጠር ልጅ ካለ የእርስዎም ልጅ ቢሆን፡ ስልክ ይደውሉ፡

**የDoCS** መስመር 132 111 (24 ሰዓት፡ በሳምንት 7 ቀን).

በቤት ውስጥ ሁከትና ጸብ የሚሰቃይ ወይም የተፈጠረውን ጸብ ለመሸሽ ሲል በአፋጣኝ መጠለያ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ከ**DoCS** ዕርዳታ ማግኘት ይችላል። ስልክ፡

**ዶመስቲክ ቫዮሌንስ ሄልፕ ላይን (Domestic Violence Help Line)፡**
1800 656 463 (24 ሰዓት፡ በሳምንት 7 ቀን).

አስቸኳይ የገንዘብ ዕርዳታ፣ የመጠለያ ቦታ፣ ምግብና ልብስ ለማግኘት የሚከተለውን ድርጅት ይጠይቁ፣

**ሴንት ቪንሴንት ደፖል ሶሳይቲ (St Vincent de Paul Society)፣**
Cnr of West and Thomas Sts. Lewisham 2049 ስልክ፣ 9560 8666

## የቤተሰብ መዋለ ሕፃናት

**DoCS** በኒው ሳውዝ ዌልስ የሚገኙ የቤተሰብ መዋለ ሕፃናት አገልግሎቶችን ይቆጣጠራል። ይህም ለትምህርት ላልደረሱ ሕፃናት መዋያ፣ ለሙሉ ቀን መዋያ፣ ከትምህርት ሰዓት በፊትና በኋላ ለመቆያ፣ ተ/ቤት ዝግ ሲሆንና በማንኛውም ጊዜ ሁሉ የሚጠቀሙበት ይሆናል። ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ወደሚከተለው ክፍል ይደውሉ

**Children's Services Switchboard:** ስልክ፣ 9557 0900 ወይም 1800 803 820

TPV ያላቸው ሰዎች ልጆቻቸውን በሕፃናት መዋያ ከማስመዝገባቸው በፊት የኮመንወልዝ የሕፃናት መዋያ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን መቻላቸውን **Centrelink**ን በመጠየቅ ማወቅ ይችላሉ።

## ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ ወጣት ስደተኞች የሚሰጥ ዕርዳታ

ቤተሰብ ሳይኖሯቸው ወደ አውስትራሊያ የሚመጡ ዕድሜአቸው 18 ዓመት ወይም ከዚያ በታች የሆኑ ስደተኞች ኑሮ ለመጀመር የሚያግዛቸውን አገልግሎቶች የሚያመቻች ዕርዳታ ያገኛሉ፣ እንዲሁም የሕክምና፣ የፋይናንስ አገልግሎትና ድጎማ፣ የትምህርት እና/ወይም የሥራ እገዛ ያገኛሉ። ስደተኛ ልጆች "የተነጠሉ" ወይም "ብቸኞች" ሊሆኑ ይችላሉ።

# የተነጠሉ የሚባሉት ስደተኛ ልጆች ወላጃ ሳይሆን አዋቂ የሆነ የቀርብ ዘመድ ይዟአቸው ወደ አውስትራሊያ የመጡ ናቸው። ለእነዚህ ተነጥለው ለሚመጡ ልጆች **DoCS** ለስድስተ ወር ያህል የመኖሪያና ሌሎች አገልግሎቶችን ይሰጣቸዋል። ለችግር እንዳይጋለጡና ከመኖሪያ ቤታቸውም ለቀው እንዳይወጡ የእገዛው ጊዜ እንደአስፈላጊነቱ ሊራዘም ይችላል።

# ብቸኞች የሚባሉት ስደተኛ ልጆች ወለጅ ወይም ዕድሜው 21 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ዘመድ ሳይዛቸው ብቻቸውን ወደ አውስትራሊያ የመጡ ናቸው። **DoCS** እነዚህን ወጣቶች -ከቤተሰቦቻቸው

ለተፈናቀሉ ከብካቤ መስጠት- በሚለው ፕሮግራሙ ስር ድጋፍ ያደርግላቸዋል። ለወጣቶቹ ተስማሚ የሆነ አሳዳጊ ተፈልጎም ከቤተሰቡ ጋር እንዲኖር ይደረጋል። አሳዳጊዎች ብቃት አላቸው ተብሎ የታመነባቸው፣ ስልጠና ያገኙና **DoCS** የፋይናንስ ድጋፍ የሚሰጣቸው ናቸው።

የማደጎ ልጆችን መንከባከብ ከቤተሰቦቻቸው ጋር አብሮ ለመኖር ያልቻሉ ልጆችንና ወጣቶችን **DoCS** የሚረዳበት ዋንኛው መንገድ ነው። ወጣቶች ወደ ቤተሰቦቻቸው ተመልሰው መግባት ካልቻሉና ቢመለሱም ደህንነታቸው አሳሳቢ ከሆነ የማደጎ አሳዳጊዎች ወይም ጊዜያው የማረፊያ ቦታዎችን **DoCS** ያዘጋጃል። የ**DoCS** ዓላማ በተቻለ መጠን ልጆችን ከወላጆቻቸው ጋር መልሶ ማዋሃድ ነው። ስለሆነም ብዙዎቹ የማደጎ ቤቶች ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው። ስልክ በመደወል

**DoCS Helpline 132 111**

(24 ሰዓት፣ በሳምንት 7 ቀን).

## ገንዘብ

TPV ያላቸው ሰዎች ስራ ያልያዙ ከሆነ ከመንግስት የገንዘብ እርዳታ ያገኛሉ። ይህንን ክፍያ የሚፈጽመው የመንግስት አካል **Centrelink** በመባል ይጠራል።

**Centrelink**ን ለማግኘት ስልክ ይደውሉ፤

131 202 (በአማርኛ ያሚያናግርዎት ያገኛሉ)

131 021 (ቀጠሮ ለመያዝ ይችላሉ)

ከጠዋቱ 8:00 am እስከ 5:00 pm ድረስ ከሰኞ እስከ አርብ (ከበዓል ቀኖች ውጪ) ይደውሉ።

## መረጃ

TPV ላላቸው ስደተኞች እርዳታ ሊያደርጉ የሚችሉ ብዙ የኮምዩኒቲ ድርጅቶች አሉ። ስለሚሰጡት አገልግሎት ለመረዳት የሚከተሉትን ቦታዎች ይጠይቁ።

**House of Welcome**
140 Wattle St. Carramar 2163
ስልክ፤ 9727 9290

**STARTTS**
44-50 Auburn Rd. Auburn 2144
ስልክ፤ 9646 6666

**The Asylum Seekers Centre**
38 Nobbs St. Surry Hills 2010

ስልክ፡ 9361 5606

**<u>ስለኢሚግሬሽን ምክር ለመጠየቅ</u>**

የመቆያ ቪዛ ለማራዘም ማመልከት ሲፈልጉ የሚከተለውን ያነጋግሩ፤

**Refugee Advice and Casework Service**
Suite 8C, 44-56 Kippax St. Surry Hills 2010
በስልክ፡ 9211 4001 ይደውሉ፤

ለድንገተኛ አደጋ፡

| | |
|---|---|
| አምቡላንስ | ስልክ ቁ. **000** |
| ፖሊስ | ስልክ ቁ. **000** |
| እሳት አደጋ | ስልክ ቁ. **000** |

**<u>የእንግሊዘኛ ትምህርት</u>**

TPV ላላቸው ስደተኞች በርካታ የእንግሊዘኛ ቋንቋ መማሪያ ቦታዎች ተዘጋጅተዋል። ስለዚህ የበለጠ ለመረዳት ከፈለጉ **House of Welcome** ወይም **STARTTS**ን ያነጋግሩ (አድራሻቸው በዚህ ወረቀት ውስጥ ይገኛል)።

**<u>ስራ</u>**

TPV ላላቸው ስደተኞች ከፍተ የሆኑ ልዩ የሥራ ፍለጋ አገልግሎቶች አሉ። ስለዚህ የበለጠ ለመረዳት ከፈለጉ **House of Welcome** ወይም **STARTTS**ን (ከላይ ይመልከቱ) ማነጋገር ይችላሉ።

# ቋ ሚ የ ስ ደ ተ ኞ ች ቪ ዛ
# ( PERMANENT PROTECTION VISAS )

ስደተኞች በአውስትራሊያ ውስጥ የሚያገኙት አገልግሎት የሚወሰነው በያዙት የቪዛ አይነት ነው። በዚህ ገጽ ውስጥ የሰፈሩት መረጃዎች ቋሚ ቪዛ ያላቸውን ስደተኞች በተመለከተ የቀረበ ነው (ከእነዚህ መደቦች ቪዛ ያላቸው) (visa subclass 200,201,202,203,204 or 866)።

**<u>መረጃዎችን ስለማግኘት</u>**

ቋሚ ቪዛ ላላቸው ስደተኞች እገዛ የሚያደርጉ በርካታ ድርጅቶች አሉ። ስለአገልግሎታቸው ለመረዳት የሚከተሉት ጥሩ ምንጮች ናቸው።

**# Initial Information and Orientation Assistance Case Manager** (አውስትራሊያ እንደደረሱ ጉዳዮችን ለማስፈጸም የሚያግዙት ሰው ከሚሰጥዎት መረጃና ገለጻ) **Visa Subclass**

(ከእነዚህ መደቦች ቪዛ ያላቸው) 200, 201, 203 እና 204

# በአካባቢው ካለው **Migrant Resource Centre (MRC)** (ማይግሬንት ሪሶርስ ሴንተር ማለት የስደተኞች መገልገያ ማዕከል ነው). MRC ስደተኞችና ጥገኞች ከመጡ ከሶስት እስከ ስድስት ወሬት ውስጥ ባለው ኑሮን የመጀመርና የመረጋጋት ጊዜ በኃላ ተገቢውን አገልግሎት በመስጠት ይረዳል። የማይግሬንት ሪሶርስ ሴንተር ጽ,ቤቶች የት የት እንደሚገኙና የስልክ ቁጥራቸውን በነጩ የስልክ ማውጫ ቢዝነስ ሊስቲንግ በሚለው ክፍል ሐምራዊ በሆኑት ገጾች ውስጥ ያገኙታል።

# **A Community Settlement Services Scheme (CSSS)** (የኮምዩኒቲ ሴትልሜንት ሰርቮስስ እስኪም) ሰራተኞች። እነዚህ ሰራተኞች አዲስ የሚመጡ ስደተኞች ኑሮአቸውን ከጀመሩና ከመረጋጊያ ጊዜአቸው በኃላ አገዛ ማድረግ ይጀምራሉ። የCSSS ሰራተኛን ለማነጋገር ከፈለጉ በአካባቢዎ ወደ ሚገኘው ማይግሬንት ሪሶርስ ሴንተር/የስደተኞች መገልገያ ማዕከል (MRC) ይሂዱ።

# **Service for the Treatment & Rehabilitation of Torture & Trauma Survivors (STARTTS)**

152-168 The Horsley Drive, Carramar
ስልክ፣ 99794 1900 ወይም

Level 3, 157-161 George St. Liverpool
ስልክ፣ 8778 2000

44-50 Auburn Rd. Auburn 2144
ስልክ፣ 9646 6666

<u>**አማካሪዎች**</u>

ስቃይና መከራ የደረሰባቸውና በጦርነት ውስጥ ያለፉ ስደተኞች ነፃ እርዳታ ያገኛሉ። **STARTTS**ን ደውለው ያነጋግሩ፤
ስልክ፡ 9794 1900 ወይም 9646 6666

<u>**ስለሕክምና**</u>

ከጤና አማካሪዎች ጋር ለመመካከር፣ ምርመራ ለማድረግና ስለኒው ሳውዝ ዌልስ የጤና አገልግሎት ለመረዳት ከፈለጉ የሚከተለውን ክፍል ያነጋግሩ።

**NSW Refugee Health Service**
(የኒው ሳውዝ ዌልስ የስደተኞች ጤና አገልግሎት)
Level 2,157-161 George St. Liverpool
ስልክ፡ 8778 0770

ቼሚ ቪዛ ያላቸው ስደተኞች መንግስት የሚሰጠውን የጤና አገልግሎት እንደሚከተለው ማግኘት ይችላሉ።

**# Medicare Card (ሜዲኬር ካርድ);** ይህንን ካርድ የያዘ ሰው በነፃ ወይም በቅናሽ ክፍያ የዶክተር ሕክምናና በሕዝብ ሆስፒታሎችም ውስጥ የተወሰኑትን ሕክምናዎች በነፃ ያገኛል።

# ሐኪም የሚያዘውን መድሐኒት በቅናሽ ዋጋ ሊገዙ ይችላሉ (ሜዲኬር ካርድ መያዝ አለብዎት)

**# Health Care Card (የጤና ካርድ)፦** ዝቅተኛ ገቢ ላላቸውና ከCentrelink አበል ለሚቀበሉ የሚሰጥ ነው፦ ይህ ካርድ ያለው ሰው በተጨማሪ ሌላ የነፃ ሕክምና ያገኛል። ነፃ የአምቡላንስ አገልግሎትና እንደ አጣዳፊነቱም እየታየ በሕዝብ የጥርስ ሕክምና ክሊኒክ የተወሰኑ ሕክምናዎችን በነፃ ሊያገኝ ይችላል።

**# Health Care Interpreter Service (የጤና ጥበቃ የትርጉም አገልግሎት)፦** ለሕዝብ የጤና ጥበቃ አገልግሎት ነፃ ትርጉም ይሰጣል።

**Medicare (ለሜዲካር)፦** 132 011 ይደውሉ

በተጨማሪም አዲስ ለሚመጡ ስደተኞች ልዩ አገልግሎት የሚሰጥ ፕሮግራም አለ። በዚህ ፕሮግራም ውስጥ ሰዎች የአካልና የስነልቦና ሕክምና ያስፈልጋቸው እንደሆን ይገመግማል በሰፈራ ሂደት ውስጥም አስፈላጊው ዕርዳታ ይሰጣል።

**STARTTS Early Intervention Program**
ስልክ፡ 9794 1900 ወይም 9646 6666

## <u>ገንዘብ</u>

ቼሚ የመኖሪያ ቪዛ ያላቸው ስደተኞች ስራ ያልያዙ ከሆነ ከመንግስት የገንዘብ እርዳታ ለማግኘት ይችላሉ። ይህንን ክፍያ የሚፈጽመው የመንግስት አካል **Centrelink** ተብሎ ይጠራል።

**Centrelink**ን በስልክ ለማነጋገር ከጠዋቱ 8:00 am እስከ 5:00 pm ድረስ ከሰኞ እስከ አርብ ይደውሉ (ከበዓላት ቀኖች ውጪ)፧

131 202 (በአማርኛ ያሚያናግርዎት ያገኛሉ)

131 021 (ቀጠሮ ለመያዝ ይችላሉ)

## የእንግሊዘኛ ትምህርት

ቹሚ የመኖሪያ ቪዛ ያላቸው ስደተኞች በ**Australian Migrant English Program (AMEP)** (አውስትራሊያን ማይግራንት እንግሊሽ ፕሮግራም) በኩል የሚሰጠውን ከ510 ሰዓት የማያንስ ነፃ የእንግሊዘኛ ቹንቹ ትምህርት ለመከታተል መብት አላቸው።

**acl** በስልክ፧ 9728 4606, ወይም

**NSW Adult Migrant English Services (AMES)** (አደልት ማይግሬንት እንግሊሽ ሰርቪስስ)

Bankstown: ስልክ፧ 9205 4350

Burwood: ስልክ፧ 9744 3885

Surry Hills: ስልክ፧ 9289 9111 ያነጋግሩ።

## የቤት ቁሳቁስ

ቹሚ የመኖሪያ ቪዛ ያላቸው ስደተኞች ሉመለስተኛ ቪዛ ምድብ 866 ካላቸው በስተቀርላ አዲሱን ኑሮ ለማቹቹም እንዲረዳቸው አስፈላጊ የሆኑ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች ይሰጣቸዋል። የሚከተለውን ክፍል ያነጋግሩ፧

**Society of St Vincent de Paul** (ሶሳዪቲ ኦፍ ሴንት ቪንሴንት ዴ ፖል) Household Formation Support (HFS) (ሀውስሆልድ ፎርሜሽን ሰፖርት) ስልክ፧ 9560 8666

## በG አድራGት

የ**Department of Community Services (DoCS)** (ዲፓርትሜንት ኦፍ ኮምዩኒቲ ሰርቪስስ) ልጆችንና ወጣቶችን ከብልሹ አስተዳደገግ ወይም ከጥቃት ይከላከላል፧ የሚቀርቡ ጥቆማዎችንና ሪፖርቶችን ይመረምራል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ከወላጆች ጋር ተባብሮ በመስራት ልጆች በደህንነት ተጠብቀው ማደጋቸውን ያረጋግጣል። ስደተኞች የሚያሳድ...ቸው ልጆች ለአደጋ ተጋልጠዋል ተብሎ ከተጠረጠረ DoCS ሌሎች ልጆችንና ሣልማሶችን ከአደጋ ለመጠበቅ እንደሚያደርገው ሁሉ ተገቢውን ርምጃ በተመሳሳይ መንገድ ይውስዳል።

አደጋ ደርሶበታል ብላችሁ የምትጠረጥሩት ልጅ ካለ የእርሶም ልጅ እንካን ቢሆን፤ ስልክ ይደውሉ፤

**የDoCS የእርዳታ መስመር 132 111 (24 ሰዓት፤ በሳምንት 7 ቀን).**

በቤት ውስጥ ሁከትና ጸብ የሚሰቃይ ማንኛውም ሰው ወይም በቤት ውስጥ ያለውን ጸብ ለመሸሽ በአስቸካይ መጠለያ የሚፈልጉ ከDoCS እርዳታ ያገኛሉ፤ ስልክ ይደውሉ፤
**Domestic Violence Help Line** (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ሄልፕ ላይን)
**1800 656 463** (24 ሰዓት፤ በሳምንት 7 ቀን).

## የሕፃናት መዋያ ለቤተሰቦች

**DoCS** በኒው ሳውዝ ዌልስ የሚገኙ የቤተሰብ ሕፃናት መዋያ አገልግሎቶችን ይቆጣጠራል። ይህም ለትምህርት ላልደረሱ መዋያን፤ ለሙሉ ቀን መዋያን፤ የትምህርት ሰዓት ከመጀመሩ በፊትና ከአለቀ በ ላ የሚያገለግል የሕፃናት መዋያ፤ ትምህርት ቤት ሲዘጋ እና አልፎ አልፎ ሲያስፈልግዎት መረጃ ለማግኘት ደውለው ያነጋግሩ፤ **Children's Services Switchboard** (ቺልድረን ሰርቪስስ እስዊችቦርድ)፡ በስልክ፤ 9557 0900 ወይም 1800 803 820 ይደውሉ።

## ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ ወጣት ስደተኞች የሚሰጥ ዕርዳታ

ቤተሰብ ሳይኖሬቸው ወደ አውስትራሊያ የሚመጡ ዕድሜአቸው 18 ዓመት ወይም ከዚያ በታች የሆኑ (ልጆች) ስደተኞች ኑሮአቸውን ለመጀመር የሚያግ›ቸውን አገልግሎቶች የሚያመቻች ዕርዳታ ያገኛሉ፤ እንዲሁም የሕክምና፤ የፋይናንስ አገልግሎትና ድጎማ፤ የትምህርት እና/ወይም የሥራ እገዛ ያገኛሉ። ስደተኞ ልጆች "የተነጠሉ" ወይም "ብቸኞች" ሊሆኑ ይችላሉ።

# የተነጠሉ የሚባሉት ስደተኛ ልጆች ወላጃ ሳይሆን አዋቂ የሆነ የቀርብ ዘመድ ይዞአቸው ወደ አውስትራሊያ የመጡ ናቸው። ለእነዚህ ተነጥለው ለሚመጡ ልጆች **DoCS** ለስድስት ወር ያህል የመኖሪያና ሌሎች አገልግሎቶችን ይሰጣቸዋል። ለችግር እንዳይጋለጡና ከመኖሪያ ቤታቸውም ለቀው እንዳይወጡ የእገዛው ጊዜ እንደአስፈላጊነቱ ሊራዘም ይችላል።

# ብቸኞች የሚባሉት ስደተኛ ልጆች ወለጅ ወይም ዕድሜው 21 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ዘመድ ሳይዛቸው ብቻቸውን ወደ አውስትራሊያ የመጡ ናቸው። DoCS እነዚህን ወጣቶች -ከቤተሰቦቻቸው ለተፈናቀሉ ከብካቤ መስጠት- በሚለው ፕሮግራሙ ስር ድጋፍ ያደርግላቸዋል። ለወጣቶቹ ተስማሚ የሆነ አሳዳጊ ተፈልጎም ከቤተሰቡ ጋር እንዲኖር ይደረጋል። አሳዳጊዎች ብቃት አላቸው ተብሎ የታመነባቸው፣ ስልጠና ያገኙና DoCS የፋይናንስ ድጋፍ የሚሰጣቸው ናቸው።

የማደጎ ልጆችን መንከባከብ ከቤተሰቦቻቸው ጋር አብሮ ለመኖር ያልቻሉ ልጆችንና ወጣቶችን DoCS የሚረዳበት ዋንኛው መንገድ ነው። ወጣቶች ወደ ቤተሰቦቻቸው ተመልሰው መግባት ካልቻሉና ቢመለሱም ደህንነታቸው አሳሳቢ ከሆነ የማደጎ አሳዳጊዎች ወይም ጊዜያው የማረፊያ ቦታዎችን DoCS ያዘጋጃል። የDoCS ዓላማ በተቻለ መጠን ልጆችን ከወላጆቻቸው ጋር መልሶ ማዋሃድ ነው። ስለሆነም ብዙዎቹ የማደጎ ቤቶች ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው። ስልክ በመደወል

**DoCS Helpline 132 111**

(24 ሰዓት፣ በሳምንት 7 ቀን).

<u>ስለኢሚግሬሽን ጉዳይ ምክር</u>

**Immigration Advice and Rights Centre (IARC)** (የኢሚግሬሽን አድቫይስ ሔንድ ራይትስ ሴንተር) ኢሚግሬሽን ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ለምሳሌ፣ ቀሪ የቤተስብ አባልን ለማስመጣት (Family reunion/ፋሚሊ ሪዩኒየን) ነፃ ምክር በመስጠት ይረዳል (ስደተኛ ለማስመጣት ፎርም አያዘጋጅም)።

<u>**መኖሪያ ቤት**</u>

በቪዛ መደብ ቁጥር 200,201,203 ወይም 204 የሚመጡ ጥገኞች የማረፊያ ቤትን በተመለከተ እገዛ ያገኛሉ። እንደደረሱም የመኖሪያ ቤትና ለቤቱም ኪራይ የሚከፍሉት ገንዘብ ይሰጣቸዋል። ከ4 ሳምንት በ ላ በከፊል ሳይሆን ሙሉውን የቤት ኪራይ መክፈል ይጀምራሉ። እዚህ ከደረሱ ከ13 እስከ 26 ሳምንት ባለው ጊዜ ውስጥ ቼሚ የመኖሪያ ቤት እንዲያገኙ እገዛ ይደረግላቸዋል። ለቤት ኪራይ የገንዘብ ድጎማ ማግኘት ይችሉ ይሆናል።

በልዩ ሰብአዊ ፕሮግራም (እስፔሻል ሂውማንቴሪያል ፕሮግራም) (ቪዛ መደብ 202) ፎርም ልኮ ሰዎችን

ያስመጣ ግለስብ ጊዜያዊ ማረፊያና ቼሚ የመኖሪያ ቤት እንዲያገኙ እገዛ ማድረግ አለበት።

ቪዛ መደብ 866 ያላቸው ሰዎች የመኖሪያ ቤታቸውን እነርሱ እራሳቸው ፈልገው እንዲያገኙ ይጠበቃል።

የ**Department of Housing** (ዲፓርትሜንት ኦፍ ሃውሲንግ) ቼሚ ቪዛ ላላቸው ስደተኞች የሚከተለውን እገዛ ያደርጋል።

# Rentstart (ሬንትስታርት) ማለት ሰዎች ቤት ሲከራዩ የሚሰጥ እገዛ ነው፤ ይህም ለምሳሌ ለኪራይ ውል መያዣ (ቦንድ)፣ ለቤት ኪራይ ቅድሚያ ወይም ለእዳ ክፍያ የሚውል የገንዘብ እርዳታ ነው። አንዳንድ አጣዳፊ ሁኔታዎች ሲያጋጥም ጊዜያዊ የማረፊያ ቦታ ይሰጣል።

# በጣም ለተቸገሩና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች የSocial housing assistance (የሶሻል ሃውሲንግ አሲስታንስ) ይስጣል።

# መንገድ ተተዳዳሪ ለሆኑ ወይም ለመንገድ ተዳዳሪነት ለተጋለጡ ሰዎች አጣዳፊ የሆነ ጊዜያዊ የማረፊያ ቦታ ሊሰጥ ይችላል።

የሚከተሉትን ያነጋግሩ፧

**NSW Department of Housing**
(ኒው ሳውዝ ዌልስ ዲፓርትሜንት ኦፍ ሃውሲንግ) በአቅራቢያዎት የሚገኘውን የቤቶች አስተዳደር መምሪያ ጽ/ቤት ለማወቅ ከፈለጉ በስልክ 8753 8000 ደዉለው ይጠይቁ ወይም **TIS** (ማለትም የጽሑፍና የቃል ትርጉም አገልግሎትን) በ131 450 የነፃ መስመር ቢደዉሉ ከቤቶች አሰተዳደር መምሪያ ጋር ያገናኙዎታል፧

ለድንገተኛ አጋጣሚ፧
**The Homeless Persons' Information Centre** (ዘ ሆምለስ ፐርስንስ ኢንፎርሜሽን ሴንተር) ማለትም የመንገድ ተዳዳሪዎች የመረጃ ማዕከልን በስልክ 9265 9081 (በየቀኑ ከጠዋቱ 9am እስከ ምሽቱ 10pm ድረስ) በመደወል ያነጋግሩ።

<u>**ስራ ፍለጋ**</u>

ስራ የሚፈልጉ ስደተኞች **Centrelink** (ሴንተርሊንክ)ን መጠየቅ አለባቸው። **Centrelink**ን በስልክ ለማነጋገር ከጠዋቱ 8:00 am እስከ 5:00 pm ድረስ ከሰኞ እስከ አርብ ይደውሉ (ከበዓላት ቀኖች ውጪ)፡

131 202 (በአማርኛ ለመነጋገር ከፈለጉ)
131 021 (ቀጠሮ ለመያዝ) ይደውሉ።

## የቃልና የጽሑፍ ትርጉም

ቼሚ የመኖሪያ ቪዛ ያላቸው ስደተኞች ሰነዶችን (ለምሳሌ፡ የልደት ምስክር ወረቀት፡ የትምህርት መረጃ፡ ወዘተ...) በነፃ ይተረሣምላቸዋል። ለተለያዩ ጉዳዮችም እንዲሁ የቃል ትርጉም በነፃ ያገኛሉ። በአገልግሎቱ ለመጠቀም ደውለው

**Translating and Interpreting Service (TIS)** (ትራንስሌቲንግ ኤንድ ኢንተርፕሬቲንግ ሰርቪስ): በስልክ፡ 131 450 ያነጋግሩ

## ትምህርት

ልጆች በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ የሕዝብ ት/ቤቶች ወይም የአጭር ጊዜ የእንግሊዘኛ ቼንቼ ኮርስ በሚሰጡ ማዕከሎችና ት/ቤቶች ውስጥ ገብተው መማር ይችላሉ።

በስልክ፡ 9561 1000 ደውለው ለስምዝገባ
በስልክ፡ 9244 5324 ስለቼንቼ ማሻሻያ ፕሮግራም ይጠይቁ።

ወጣቶችና Gልማሶች **TAFE** (ቴፍ) በሚሰጠው የቼንቼና የሙያ ስልጠና ፕሮግራም መሳተፍ ይችላሉ።

የ**TAFE** መረጃ ማዕከልን በ131 601 ያነጋግሩ።

Special Humanitarian Program Entrants (እስፔሻል ሂውማኒቴሪያል ፕሮግራም) ማለትም በልዩ የርኅራኄ አስተያየት ፕሮግራም (ቪዛ መደብ 202)

ሴንተርሊንክ ስለሚሰጠው ጠቀሜታ፡ ስለሜዲኬርና ሌሎችም ስለሚስጡት አገልግሎቶች ወይም ደግሞ የመኖሪያ ቤት ከሌልዎት አንዳንድ ድጎማዎችና እገዛዎችን ለማግኘት ይችሉ ይሆናል።

**Department of Immigration and Multicultural and Indigenous Affairs**

**(DIMIA)** (ዲፓርትሜንት ኦፍ ኢሚግሬሽን ኤንድ መልቲካልቸራል ኤንድ ኢንዲጂነስ አፌርስ) (ዲሚያ)ን በስልክ 131 881 ወይም በአካባቢዎ የሚገኘውን የዲሚያ ጽ/ቤት ያነጋግሩ።

በእንግሊዝኛ ለማነጋገር ከተቸገሩ የ**Translating and Interpreting Service (TIS)** (ትራንስሌቲንግ ኤንድ ኢንተርፕሬቲንግ ሰርቪስ): በስልክ፥ 131 450 ቢደዉሉ ዲሚያን በነፃ ያገናኝዎታል። በአውስትራሊያ ውስጥ ለ12 ወራት የቆዩ ከሆነ ከCSSS (የኮምዩኒቲ ሴትልሜንት ሰርቪስስ ስኪም) ሰራተኛና በአቅራቢያዎት ከሚገኘው MRC ጽ/ቤት እርዳታ ጠይቀው ማግኘት ይችላሉ።